# የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት በአርሲ ዞን ማሳያነት

ፍሬህይወት ባዩ

**አጽኅሮተ ጽሁፍ**

*የጥናቱ ዋና አላማ፣ በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት መካከል በሰላማዊ አብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ ፎክሎሮችን ማስተዋወቅ ይሆናል። ኢትዮጵያ በብሔረሰቦቹዋ ውስጥና መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ምን እንደሚመስሉ ተጠንተው አልተገለፁም፡፡ አይታወቁም፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሆነው በአርሲ ዞን፣ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ባለው የመቻቻል እሴት ከፎክሎር አንፃር ማሳየት ነው። በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በሰላም ተከባብሮ ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል ፎክሎር ምንድን ናቸው? በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ለሰላማዊ አብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመቻቻል ባህላዊ እሴቶች በተለይ እድር፣ ጡት መጣባትና ባህላዊ እምነት ጥናቱ ያተኮረባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው። በማህበረሰቦች መካከል ያሉትን የሃይማኖት ልዩነቶች በመቻቻል የሚመሩ፣ በባህል የተደነገጉና የተቋዋቋዋሙ ለዘላቂ ሰላም መሠረትና ዋስትና ተግባራዊ ሕጎች ሆነው ይሠራሉ፡፡ ባህላዊ እሴቶቹ በተለይም በእስልምናና በትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል 'መቻቻል' የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ፣ መርህና ተግብራዊ ድርጊቶች ማለትም፡- አንዱ የሌላውን ኀልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣ መከባበርን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንና ሰላምን፣ ወዘተ፣ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡*

## 1.መግቢያ[1]

በኢትዮጵያ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ምናልባትም በዓለማችን ልዩ ባህርይ ያለው የመቻቻል እሴት ፈጥረው ለዘመናት መኖራቸውን የተለያዩ ምሁራን አጽንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ Abdullah(2012)፣ Abbink(1998)፣ Braukamper(1992)። ብዝኀ-ባህል ከሚገለፅባቸው ቅርፆች መካከል አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች በተጓዳኝ መኖራቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያ በብሔረሰቦቹዋ ውስጥና መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ምን እንደሚመስሉ ተጠንተው አልተገለፁም፡፡ አይታወቁም፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሆነው በአርሲ ዞን፣ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ባለው የመቻቻል እሴት ከፎክሎር ዕይታ አንፃር ምርምር ማካሄድ ነው። የጥናቱ መነሻ ምክንያት ኢትዮጵያ የብዝኀ-ባህል ጥንቅር ከመሆኑዋ ዕውነታ የመነጨ ነው፡፡ የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ከሚገለፁባቸው እሴቶች

[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ችግር ፈቺ ጥናቶች እንዲካሄዱ ለማበረታታት እ.ኤ.አ 2017 ዓ.ም ባወጣው የትልመጥናት ውድድር "Promoting religiouse tolerance for peaceful co-existance: the case of Arsi"በሚል ርእስ ካለፉ ትልመ ጥናቶች አንዱ ነው።

መካከል አንዱ "መቻቻል" ነው። በተለይ የሃይማኖት መቻቻል ፅንሰ-ሀሳብ በየእለቱ በሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች አማካይነት ልዩነትን አክብሮ አንድነት እንዴት ጎልቶ እንደሚወጣ ለማሳየት ጥናት ማካሄድ ዋነኛው የመነሻ ምክንያት ሊሆን ችሉዋል፡፡የጥናቱ አላማ፣ በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት መካከል በሰላማዊ አብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ ፎክሎሮችን በመለየት ለማያውቀው ማስተዋወቅ ይሆናል። በዚህ ጥናት የተመለሱ የምርምር ጥያቄዎች፣ በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በሰላም ተከባብሮ ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል ፎክሎር የትኞቹ ናቸው? የሃይማኖት መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶች የሚታዩባቸው ለውጦች አሉ ወይ? የሚሉ ናቸው።

የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው የአንድ ሀገር ህዝቦች በልዩነቶች ምክንያት ወደ ግጭት እንዳይገቡ ለመከላከል መፍትሄ ሊሆኑ ከሚችሉ መንገዶች አንዱ የመቻቻል እሴቶችን በጥልቀት የመረዳትና የማስተዋወቅ ስራ መስራት ሲሆን ለዚህ መሰረቱ ጥናት ነው። ይህ ጥናት ተጠኚው ህዝብ የፈጠራቸው፣ ያዳበራቸው እንዲሁም እየደበዘዙ ያሉ በሰላም ተከባብሮ የኖረበትን የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን በመለየት ለሌላው ለማስተዋወቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የጥናቱ ወሰን፣ መቻቻል ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ በመሆኑ ከዚህ ውስጥ በሃይማኖት ልዩነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አንድ ሆነው ተስማምተው ሲኖሩ አብሮነታቸው በሰላም በመከባበር እንደሆነ የሚያሳዩ ፎክሎሮች ላይ ብቻ ያተኩራል። የቡድኖች የልዩነት ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። ይህ ጥናት ግን በሃይማኖት የተለያዩትን ቡድኖች ብቻ ይመለከታል።

## 2.የጽንሰ ሀሳብ መነሻ እና የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ክፍል የጥናቱን መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ የሚመለከት ብያኔ እና ጥናቱ ግብአት ያደረጋቸውን መረጃዎች ከየት በምን መንገድ እንዳገኛቸው የቀረበበት ነው። መቻቻል የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከተሰጠው የተለያዩ ብያኔዎች መካከል ለዚህ ጥናት የተሻለ የተባለውን ብቻ በመምረጥ በአጭሩ የተገለጸበት ክፍል ነው። በቅድሚያ የጽንሰ ሀሳብ መነሻ የሆነውን "መቻቻል"ን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 2.1 የጽንሰ ሀሳብ መነሻ_ መቻቻል(Tolerance)

እንደ ዩኒስኮ የመቻቻል ብያኔ "መቻቻል የሞራል ግዴታ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ህጋዊ ቅድመ ሁኔታም ጭምር ነው። ለሠላም መስፈን አስፈላጊ ምግባር የሆነው መቻቻል የጦርነት ባህልን በሰላም እሴት ለመቀየር የራሱን አስተዋጽዎ ያደርጋል። መቻቻል፤ ሽንፈት፣ ውርደት ወይም ጥቅምን አሳልፎ መስጠት አይደለም። መቻቻል ከሁሉ በላይ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶችንና የሌሎችን መሠረታዊ ነጻነቶች እውቅና ከመስጠት የሚመነጭ አዎንታዊ አመለካከት ነው (UNESCO፣ 1995)።

መቻቻል በአንድ ሰው ፈቃደኝነት የተለያዩና ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን የመቀበል በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን እምነት ወይም አመለካከት ላይ እውነተኛ መሆን፣ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ፍርድ ከመስጠት መቆጠብ ማለት መሆኑን ያስረዳል። "መቻቻል" ሥነ-ምግባር ወይም ግብረ-ገብ ሲሆን

የአንዱ ወገን እምነት "እውነት የሌለው ውሸት ወይም በተቃራኒው ነው ብሎ ትንተና ወይም ገለጻ ከመስጠት የተቆጠበ ነው" በማለት መቻቻልን ይገልጸዋል (Murphy 1997፡ 607-608)።

የመቻቻል ፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ከመልካም አተያይ ጋር የተቆራኘና በተግባር የሚገለጽ የማህበራዊ ግንኙነት መስተጋብር ነው። መቻቻል ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ቡድንና እስከ ሀገር እንዲሁም በመንግሥታት መካከል የሚገለፅ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። መቻቻልን በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ እንዲህ ነው ብሎ ለመተንተን ከመሻት ይልቅ በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ባለ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት አስተውሎት ላይ ተመስርቶ የሚጠና ነው፡፡

መቻቻል ከሚታይባቸው መካከል የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ ቡድኖች ሲሆኑ ይህም የሃይማኖት መቻቻል በሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚታይ ይሆናል። በሃይማኖት መቻቻል ብያኔ "የሌሎችን ሃይማኖት ከራሳችን ሃይማኖት ጋር በማንኛውም መለኪያ ብንመዝነው ወይም ብናነፃጽረው 'መጥፎ ነው!' የምንልበት መለኪያ የለንም"(Newman 1978፡ 179)። በማለት የእኔ ሃይማኖት ትክክል ነው የሌላው ልክ አይደለም የሚለውን መለኪያ ሳያነሱ የየራስን ሃይማኖት የያዙ ቡድኖች አንድ የሚሆኑበት የጋራ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ማህበራዊ ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረ-ሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚጠና ነው። መቻቻል የምንለው ተቀራርበው ወይም አብረው በሚኖሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል በተግባር የሚገለጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው።

አብሮነት ሁለት የተለያዩ ቡድኖች አብረው ሲኖሩ ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት የሚፈጥሯቸው የጋራ ጉዳዮች ሲጎዳኙ ያለው ግንኙነት ሰላማዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው። የአብሮነት ጽንሰ ሀሳብ ከመቻቻል ጽንሰ ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው። መቻቻል የምንለው እና በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚገለጽን አንዱ ለሌላው ያለውን አክብሮት በተለይም ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ጉዳይ አብሮ መሆንን የሚያሳይ ነው፡፡ ሰዎች አብሮ በመኖር ልምድ ተመክሮ ያገኛሉ። በተመክሯቸው ምን መሥራትና አለመሥራት እንዳለባቸው ምርጫ በማድረግ መልካም ወደ ሆነው ሁሉ ምን እንደሚመራቸውና እንደማይመራቸው ያውቃሉ። "አብሮነት" የተሻለ የኑሮ ግንኙነት ስልት ለመፍጠር ማህበራዊ መተሳሰብን ለማጠናከርና አካባቢን ምቹ ለማድረግ የሚያግዝ የመቻቻል ባሕርይ ነው(Jhon 2001፡ 64)። መቻቻል የግድ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው። በመሆኑም አብሮነት እነዚህ ቡድኖች በሰላም አብረው ለመኖር አንዱ የሌላውን እምነትና ድርጊት አክብሮ መገኘትንም ያስገነዝባል።


**2.2 የጥናቱ ዘዴ**

የመቻቻል ባሕርያትን ለመረዳትና ባህላዊና ማህበራዊ የመከሰቻ ገጽታዎችን ለመለየት በይበልጥ በአውድ ላይ የተመሠረቱ የአይነት (qualitative) ወይም የትርጉም (interpretative) መረጃዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከተጠኚው ህዝብ እይታ አንፃር ወጥ ወይም አዲስ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል "ቀዳማይ" (Primary) የመረጃ ምንጭ አንዱ ነው። ሁለተኛው፣ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ሲሆን ከተለያዩ ጽሁፎች እና ተዛማጅ ምንጮች የሚገኝ ነው፡፡ በሁለቱም

የመረጃ ምንጮች አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ ሂደት ውስጥ ከመስክ መረጃ ለማሰባሰብ ወደ ህዝቡ ሲገባ 'ውስጣዊ እይታን' (Emic, insider's view) እና 'ምሁራዊ እይታ' (Etic, outer's perspective) ሚዛናዊ ማድረግ ይጠበቅበታል (Fetterman 2009:32)፡፡ በዚህ ጥናት ሁለቱን እይታዎች ሚዛናዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ከመስክ መረጃ ሲሰበሰብ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። እነዚህም ምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ናቸው።

**3.አካባቢያዊ ዳራ**

ለጥናቱ የተመረጠው ኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ነው። በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳና የበቆጂ ከተማ አስተዳደር ናቸው። የአርሲ አስተዳደራዊ መዋቅሩ በ24 የከተማ አስተዳደርና በ497 የገጠር ቀበሌዎች የተከፈለ ነው። አዋሳኞቹም በምስራቅ ሀረርጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ሸዋ፣ በደቡብ ባሌ ዞን፣ በምእራብ ደግሞ ምእራብ አርሲ ይገኛሉ። አርሲ ዞን በካርታ[2] የሚከተለውን ይመስላል።




---
[2] ካርታው ከዚህ ቀደም በአርሲ ዞን በ2009 ዓ.ም ለተደረገ ጥናት የተዘጋጀ ነው።

ማእከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ ባደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት በአርሲ ዞን የሚኖረው ህዝብ 2,957,817 ይሆናል (CSA 2007-2008)። ከዚህ ውስጥ ወንዶች 1, 483,934 ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 1,473,883 እንደሆኑ ያመለክታል። የከተማና የገጠር ነዋሪ ስብጥር የገጠሩ ነዋሪ 2, 591,066 ሲሆን የከተማ ነዋሪው ደግሞ 366,751 ነው። ከዚህ ውስጥ በሌሙና ቢልቢሎ የሚኖረው ህዝብ ብዛት 181,789 እንደሆነ ይገልጻል። ከነዚህ መካከል የገጠር ነዋሪ 158, 459 ሲሆን 23,330 የከተማ ነዋሪዎች ናቸው። የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር በ2002 ባደረገው ቆጠራ ደግሞ አጠቃላይ የህዝቡ ብዛት 204, 458 ሲሆን ወንዶች 105, 371፣ ሴቶች ደግሞ 10,381 ይሆናሉ (የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር 2002፡ 15)።

የወረዳው ነዋሪዎች በ1998 ዓም በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን(የኢ.ኦ.ተ.ቤ)፣ የእስልምናና የፕሮቴስታንት[3] ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በጥናቱ ከመስክ በተገኘ መረጃ ከቆጠራው በኋላ በአካባቢው የተዋወቁ በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ጥቅል ስም የሚጠሩ እና ከዚህ ውጭ የሆኑም እንዳሉ መረጃ ሰጪዎች እንዲሁም በምልከታ የተገኘው መረጃ ያሳያል። "በ2003 ዓ.ም ቃለ-ህይወት ቤ/ን ተመሰረተች። ህይወት ብርሀን ቤ/ን ደግሞ በ1997/1998 አካባቢ ተመሰረተች። የህዋርያት ቤ/ን ደግሞ (የህዋሪያት ቤ/ን ከስድስቱ ጋር ህብረት የላቸውም፤ የአምልኮ ስፍራቸውም ለብቻ ነው።) በ1990ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ተመሰረተ።[4]

*"በተለይ የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች የሚከተሉትን ሃይማኖት በተመለከተ "ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?" ተብለው ሲጠየቁ ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ብለው ይመልሳሉ። ሆኖም ከዚሁ ጎን ለጎን ባህላዊ የሆኑ እምነቶችንም ሲከተሉ ይታያሉ።*

*የወረዳው ነዋሪዎች የሃይማኖት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ህብረት ይፈጥራሉ። ማህበራዊ ግንኙነቱን ለመፍጠርም ሆነ የተመሠረተው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረውና መሠረት እንዲይዝ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ሚናቸው ተመጣጣኝ ነው። ማህበራዊ መስተጋብሮቹ በኑሮ ውስጥ አንዱ ወደ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች በመሄድ ይገናኛሉ። ኢጋጣሚዎቹም ባህላዊ መድሃኒት በመስጠትና በመቀበል፣ ኢድር አብሮ በመግባት፣ ባህላዊ የእምነት ስፍራዎች በጋራ የሚከወኑ ክዋኔዎች ላይ በመካፈል እንዲሁም የተጣላን በማስታረቅ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚገናኙባቸው ኢጋጣሚዎች ናቸው።*

[3] ፕሮቴስታንት በሚባለው ትልቅ ጥላ ስር ተካተው የሚጠሩት፡- ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን፣ ጴንጤ ቆንጤ (Pentecostal)፣ መካነ እየሱስ (Luteran)፣ መጥምቃዊያን፣ አንጀሊካን(Anglican)፣ ፕሬስቢተሪያን ቤተክርስቲያን (Presbyterian)፣ መሰረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ህይወት፣ ወዘተ(እስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ 2007፣ 71) በእዚህም ጽሁፍ ውስጥ ከዚህ በኋላ ፕሮቴስታንት በሚለው መጠሪያ የሚጠቀሱት እነዚህ ናቸው።

[4] ምንጭ፡- መጋቢ ብሩክ አለሙ፣ እድሜ 46፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የሌሙና ቢልቢሎ ሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተ-ክርስትያን አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም የወረዳው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተዳዳሪ(ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 19/2009)፡፡

**4.የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት**

በዚህ ክፍል ከመስክ የተሰባሰበ መረጃ የቀረበበት ነው። በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ለሰላማዊ አብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመቻቻል ባህላዊ እሴቶች በተለይ እድር፣ ጡት መጣባትና ባህላዊ እምነት የቀረበበት ነው። ማህበረሰቡ እነዚህን ባህላዊ የመቻቻል እሴቶች መገለጫ ካለፈው ትውልድ ተቀብሎ ዛሬ ይከውነዋል፣ ይኖረዋል። ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድም በተለይ እድር ዛሬም ጠንካራ መሰረት ያለው ሲሆን ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነት ከዋኔው እየቀነሰ ይገኛል። ሆኖም ዛሬ ድረስ እነዚህን ባህላዊ እሴቶች በመኖር በተግባር በማሳየት ያስተዋውቋቸዋል።

**4.1 እድር**

ዕድር የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ባህላዊ-ማህበራዊ ተቋም ነው። የዕድር አባላት በመተሳሰብ የሚረዳዱበት፣ የሚተጋገዙበት፣ የሚማማሩበት፣ አንዱ የሌላውን ችግር የሚካፈልበት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ አንድ እድር ሲመሰረት መሥራቾቹ ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡ ፍላጎቱ የሚመጣው በመቀራረብና አንዱ ሌላውን በማክበር በመተሳሰብ አንዱ ለሌላው መኖር እውቅና በመስጠት የሚጠነክር ነው፡፡ዕድሮች በአባላት የመኖሪያ ሠፈር፣ በጾታ ላይ መሠረት አድርገው ይደራጃሉ ወይም ይዋቀራሉ፡፡ የወንድ፣ የሴት፣ የሰፈር፣ ትልቁ የከተማ የገጠር የሚሉ የዕድር ዓይነቶች ዋና ትኩረት አንድ ሰው ሲሞት አስክሬኑን በክብር መሸኘት፤ ሀዘንተኞችን ማጽናናት፣ በጉልበትና በገንዘብ መርዳት፣ ለለቀስተኛ እንግዶች ምግብ ማዘጋጀትና ማስተናገድ ነው።

ቀደም ሲል ዕድሮች በቃል በሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ነበሩዋቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን እያንዳንዱ ዕድር በፅሁፍ የሰፈረ መተዳደሪያ ደንብ አለው፡፡ ዓላማና ደንቦችን በፅሑፍ ማስፈር የተለመደ አሠራር እየሆነ ነው፡፡ በየቀበሌዎቹ የተመሠረቱ ዕድሮች መተዳደሪያ ደንቦችና ዓላማዎች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ልዩነታቸው በአደረጃጀት ወይም በአወቃቀርና በአባላት ብዛት አንዱ ከሌላው ይለያያሉ፡፡ ደንቦቹም ስለ ዕድርተኞች አባልነት መሥፈርቶች፣ የአባላት መብቶችና ግዴታዎች፣ ስለ ዕድር ዓይነቶች፣ ተግባርና አገልግሎት፣ ስለ መሪዎች ወይም ስለ አስተባባሪዎች በዝርዝር የሚገልፁ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ደንቡን ሲያወጡም አባላቱ በረቂቁ ላይ ተወያይተው፣ የሚጨመረውን ጨምረው፣ የሚሻሻለውን አሻሽለው፣ መተዳደሪያ ደንብ አድርገው ማጽደቃቸውን ሁሉም በፊርማቸው ያረጋግጣሉ።

ዕድር አንድ ዋነኛ የመቻቻል ባሕርያት የሚገለፅበት የማህበራዊ ግንኙነት ተቁዋም መሆኑን፣ በተለይም ደግሞ በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል በአብሮ መኖር ሂደት የተገነባው የመቻቻል ባህል እጅግ በጣም የላቀ፣ ልዩ ባሕርይ፣ ያለው ነው፡፡ ዕድሮችም በተለያዩ ቅርፆች፡- በፆታ፣ በሙያ፣ ወዘተ፣ የተደራጁ፣ ነገር ግን፣ ተመሳሳይ ሕገ-ደንቦች ያሉዋቸው፣ ዓላማቸውም በሃይማኖት ልዩነት ላይ ያልተመሠረተ በሀዘን በደስታ ለመረዳዳት የተመሰረተነው።

እነዚህ እድሮች ከ1940ዎቹ መጀመሪያ እስካሁን የዘለቁ ናቸው። ከስልሳ አመት በላይ እድሜ ካለው የመጀመሪያው እድር ጀምሮ እስካሁን የነበረው ቀጥሎ አዳዲስ እየተመሰረቱ በርካታ እድሮች ለተመሳሳይ አላማ በተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ዘልቀዋል። በተለይም በኢ.ኦ.ተ.ቤ እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ መቻቻሉ እስካሁንም እንደነበረ ነው።

መቻቻል እንዳለ ሁሉ አለመቻቻል በእድርተኞች ውስጥ የተከሰተባቸው አጋጣሚዎች አሉ። የዕድሮቹን ብዛት እና የእድርተኛው ቁጥር ሲታይ አለመቻቻሉ ጥቂት የሚባል ነው። ላለመቻቻሉ ምክንያት የሆነው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው መተዋወቅ ሲጀምር ቀደም ሲል የሌላ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑትን ግለሰቦች ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት መቀየርን ለመቃወም ሲባል የተፈጠረ እንደሆነ ከ19 41ዓ.ም ጀምሮ እድርተኛ የሆኑት መረጃ ሰጪ ይጠቁማሉ[5]። ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በተያያዘ የተከሰተባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩና እንዲያውም የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን ወደ እድር እንዳይገቡ የሚያደርግ መስፈርት ሁሉ ተካቶ ነበር። ለምሳሌ የአንዱን እድር ደንብ እንመልከት

በነባር እና አዲስ በተመሠረቱ የተለያዩ ዕድሮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን እና/ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆንን የሚያበረታቱ ወይም የግድ የሚጠይቁ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በበቆጂ ከተማ የሁለተኛ ሽንጎ የመተዳደሪያ ውስጠ ደንብ፡-የማህበሩ አባል መሆን የሚችለው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለበት።…ከሁለቱ እምነቶች ውጪ የሚከተል ወደ ዕድሩ መግባት አይፈቀድለትም። ነባር አባል የነበረበትን ሃይማኖት መቀየር ካስፈለገው ዕድሩን በፈቃዱ እንደለቀቀ ተቆጥሮ ከዕድሩ ይሰረዛል" (1996 አንቀፅ 3፣ 4)።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዕድሮች ሕገ-ደንቦች ውስጥ ይህ መመዘኛ በተለይም ከ1982 ዓ.ም በኋላ የመጣ ነው። መመዘኛውን ለማውጣት አስገዳጅ ምክንያት የሆነው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ወደ አካባቢው መምጣት ነው፡፡ የእነዚህ ደንቦች በዕድር ውስጥ መካተት ዋንኛ ምክንያት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው እንዳይስፋፋ ለመግታት ሲባል ነው[6]፡፡ በዚህ አጋጣሚም ቀድሞም በዕድር ተሳስረው፣ ተሳስበውና ልዩነታቸውን አክብረው በሰላም ይኖሩ የነበሩት የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ይበልጥ አንድነታቸውን አጠናከሩ፡፡

መቻቻል በሂደት የሚገነባ ተግባራዊ እሴት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁት ችግሮች ተከስተው ከቆዩ በሁዋላ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ከልምድ በመማር በአንድ ላይ ሆነው የአንድነት እድሮችን በማቁቁዋም እርምት ማድረጋቸውን የመስከ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ በመሆኑም ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ የዕድር የአባልነት መስፈርቶች

---

[5] ምንጭ፡-አቶ አህመተ ዘማርያም፣ እድሜ 94፣ (ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2009)

[6] አስተዳዳሪምንጭ፡- መጋቢ ብሩክ አለሙ፣ (ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 19/2009)፡፡

እየተለወጡ በፕሮቴስታንትና በእስልምና ተከታዮች፣ በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል የነበረው አለመግባባት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረገበ መጥቶ የአንድነት ዕድሮች ተቋቁመዋል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ የተለያየ ሀይማኖት ተከታይን ያካተተ እድር በ2003 ዓም ተቋቁሟል[7]። ማህበረሰቡ ከልምድ በመማማር የመቻቻል መንገዶችን በመከተል ከልዩነት ወደ አንድነት ዕድሮች በመሰባሰብ የአብሮ መኖርን የወል ጥቅሞች እየተካፈለ ይገኛል፡፡

ዕድሮችን በጋራ የሚመሠርቱበት ዋና አላማም በክፉ በደግ በመካከላቸው ለመረዳዳት፣ ለመተጋገዝ፣ ለመደጋገፍ፣ ወዘተ፣ ነው፡፡ እነዚህ እሴቶች ደግሞ መቻቻል ከሚያካትታቸው ባሕርያት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሞት በሰው ልጅ ሕይወት የማይቀር ተፈጥሯዊ ግዴታ ነው፡፡ ቀጠሮ የለውም፡፡ በድንገት ሲመጣ የሰው ልጅ አጋዥ ያስፈልጋል። በማህበረሰቦቹ ባህል አንድ ሰው ሲሞት በብዙ ሰው አጀብ አስከሬን ወደ መቃብር በክብር ይሸኛል። ከመቃብር መልስ እስከ ሶስት ቀን የሟችን የቅርብ ዘመዶች ለማጽናናት ወዳጅ ዘመድ አብሮ ይቆያል። ያዝናል። ያስተዛዝናል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ኅረቤት የእንግዳ መሸኛ መጠለያ ይሠራል። ያስተባብራል። ገንዘብ በማዋጣት ወጭውን ይጋራል። የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የሙስሊምና ክርስቲያን ማህበረሰቦችም አንዱ ሌላውን ተቀብሎ አብረው በመኖር የሚረዳዱበት ዕድር ሰበበ ምክንያት ይህ ነው፡፡

**4.2“ጡት መጣባት”**

ጡት መጣባት ሃይማኖታዊ ገደብ የሌለበት የሥጋ ዝምድና በሌላቸው ሁለት ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች መካከል በፈቃደኝነት የዝምድና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ትውፊታዊ ደንብ ነው፡፡ ጡት ጠቢ የሚባለው ዝምድናውን ፈልጎ የጠየቀው ግለሰብ ሲሆን ተጠያቂው ወይም ተለማኙ ደግሞ ተጠቢ ይሆናል። ጡት ልጥባ ወይም ልዛመድ ብሎ የሚጠይቀው ዝምድናውን የሚፈልገው ወገን ሲሆን ለዚህም በባህላዊ ደንቡ መሠረት አስፈላጊ የሆነውን ክዋኔ መፈጸም ይኖርበታል። ዝምድናው ሲገለጽ ዘመድ ነን ለማለት “ጡት ነን ወይም ጡት ናቸው” ይባላል። እከሌ “የእኔ ጡት ነው” ከተባለ ዘመዴ ነው ማለት ሲሆን በስጋ ዝምድና ሳይሆን በባህላዊ መንገድ የተዛመዱ እንደሆኑ ይታወቃል። ይህንን ባህላዊ ልማድ የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ ያደረገው በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል መከወን መቻሉ ነው።

የጡት ልጅና የጡት አባት የሚሉት ጽንሰ ሀሰቦች በአማርኛ መዝገበ ቃላት የሚፈታበት መንገድም ተመሳሳይ ነው። የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃል “ጡት ተጣባ” የሚለውን የጡት ልጅና የጡት አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመዱ “ጡት አጣባ” የሚለውን ደግሞ “የጡት ልጅ አደረገ” በማለት ይተረጉመዋል። እንዲሁም የጡት ልጅ ከትውልድ ሀረግ ውጭ የሆነና የአንድ ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሲሆን የጡት አባት ደግሞ በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ሰው ማለት ነው፡፡

[7] “ሃይማኖት አልባ ዕድር፣ አንድነት አስረኛ ሸንጎ” ተብሎበ2003 ዓ.ም ተቋቋመ።(ምንጭ፡-አቶ መስፍን ተካ እድሜ 49፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የእድሩ ሰብሳቢ (ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 20 2009)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ የአማርኛ መዝገበ ቃል ደግሞ ይህንኑ ሀሳብ ሰፋ በማድረግ እንደሚከተለው ብያኔ ሰጥቷል። "ጡት ተጣባ" የጡት ልጅና አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመዱ። "የጡት ልጅ" ማለት ደግሞ ከትውልድ ሃረግ ውጭ የሆነና የአንድ ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሰው ሲለው "የጡት አባት" የሚለውን ደግሞ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ) በማር የተነከረ ጣቱን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ሰው" (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962) በማለት ይበይነዋል።

በዚሁ የአማርኛ መዝገበ ቃል "የጡት እናት" የሚለውን ቃል ፍቺ በመስጠት ሴትም የጡት እናት እንደምትሆንና በዚህ ባህላዊ ልማድ ዝምድና እንደምትመሠርት ቢጠቀምም በዚህ ጥናት የተገኘው መረጃ ግን ጡት መጣባት በወንዶች መካከል የሚከወን ባህላዊ ልማድ እንጂ ሴቶች ወይም ሴትና ወንድ ይህንን ሥርዓት እንደማይፈጽሙ ያሳያል። ዝምድናው የተፈለገው የሚጠባው ግለሰብ ጡትም ማር ተቀብቶ እንደሚከናወን ከመረጃዎች ለመረዳት ይቻላል።

ጡት መጣባት ከጉዲፈቻ ተመሳሳይነት ቢኖረውም የተለየ የዝምድና መንገድ ነው። በሃይማኖት የተለያዩ ሁለት ቤተሰቦች በጉዲፈቻ አማካይነት ዝምድና መፍጠር የተለመደ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ግን ልማዱ በአንደኛው ቤተሰብ ዘንድ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የተደረገ ሆኖ በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት አስተያየት ስለሚታይ የሚበረታታ አለመሆኑን ነው። የዚህ አንድምታም ዝምድናን ከማጥበቅ ይልቅ ልዩነቱን አለማክበርና ቅሬታን በእስልምና እና በክርስትና ሃይማኖት መካከል የሚፈጥር ያደርገዋል።

የመዛመዱ ምርጫ በሦስተኛ ወገን የሚወሰን ሳይሆን በራሱ በግለሰቡ ነው፡፡ ጡት ጠቢውም ተጠቢውም (በሁለት ግለሰቦች) መካከል የሚመሠረት ዝምድና በቤተሰቦቻቸውና በቤተ-ዘመድ መካከል የጸና ይሆናል። ዝምድናው የሚፈጸመው ለረጅም ጊዜ በሚተዋወቁ በሚግባቡና በሚዋደዱ ወገኖች መካከል ያለው ወዳጅነት ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋል[8]።

ዝምድናው የሚፈጸመው ለረጅም ጊዜ በሚተዋወቁ በሚግባቡና በሚዋደዱ ወገኖች መካከል ያለው ወዳጅነት ጠንካራና ዘላቂ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋል። የጡት መጣባት ዋነኛ ምክንያት በተለያዩ ወገኖች መካከል ጥብቅ ዝምድና ለመፍጠር ሲባል ነው፡፡ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የሚከናወነው የጡት መጣባት ባህል በአብዛኛው የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ነው። ተመሳሳይ ሃይማኖት በሚከተሉ ማህበረሰቦች አባላት መካከልም ይካሄዳል። በእስልምና እና በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ተከታዮች መካከል ጋብቻ ስለማይፈቀድ ሁለት ወዳጅነት ያበጁ ቤተሰቦች የጋብቻ ያህል ለመዛመድ ጡት መጣባትን ይመርጣሉ[9]። የዝምድና ሥርዓቱ ጋብቻ ለመፈጸም ከልመና ጀምሮ እስከ ጋብቻው ዕለት የተለያዩ ሂደቶች እንዳሉት ሁሉ ጡት መጣባትም እንደዚሁ ሂደት አለው።

የጡት መጣባት ሥራተ-ክዋኔ የሚፈፀመው በጡት አባት ቤት ነው። በቀጠሮው ዕለት የጡት አጥቢው ድግስ ደግሶ፣ ዘመዶቹን በሙሉ ጠርቶ፣ ጡት ጠቢውን ይጠብቀዋል። በዚህ ሥነ-

[8] ምንጭ:- አለሙ ባጫ(ቃለመጠይቅ መጋቢት 23 2009)።
[9] ምንጭ:-ጀማል ዋቤ(ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 6 2009)።

ሥረዓት ላይ የሚታደሙት ለዝምድና የተፈላለጉት ግለሰቦች የቅርብ ዘመዶች እንዲሁም ለዝምድናው መሳካት የደከሙ ሽማግሌዎች ናቸው።

የጡት አባት የጡት ልጁን ከአብራኩ ከወጡ ልጆቹ፣ ከስጋ ዘመዶቹ ለይቶ ላያይ፣ ችግሩን ችግሩ አድርጎ ሊወስድ፣ ልጁም እንደዚሁ የጡት አባቱን ልክ እንደ ወላጅ አባቱ፣ ዘመዶቹንም እንደ ሥጋ ዘመዶቹ አድርጎ የሀዘን የደስታ ተካፋይ እንዲሆን የሚያበቃ ቃል የሚገቡበት ነው። በሥነ-ሥርዓቱም ላይ የተገኙት የጡት አባት ወገኖችም እንደ ሥጋ ዘመዳቸው ሊቆጥሩት ቃል ይገባሉ። ዝምድናው ሲመሰረት በአብዛኛው የእድሜ ገደቡን ስናይ እራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ወጣቶች እና ጎልማሶች ዝምድናውን ይጠይቃሉ። አንድ ወጣት አባት እናቱ በህይወት ኖሩ አልኖሩ ከጡት ዝምድናውን ለመመስረት አያግዳቸውም። ሆኖም ወላጅ አባቱ በህይወት ካላ የጡት አባት የፈለገው ልጅ አባቱን ከሌሎች ሽማግሌች ጋር ሆኖ እንድያማልደው ይልከዋል። ክዋኔው ሲፈጸምም እናት አባት አያት ካሉ ይገኛሉ። በመስክ መረጃ ጡት ልጅ ያላቸውን ብዛት ስንመለከት ትልቁ ስምንት[10] ሲሆን ትንሹ አንድ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከአንድ በላይ የጡት ልጅ ሊኖረው ይችላል።

የጡት መጣባት ሥርዓት ሲፈጸም የሚዛመዱት ወገኖች የሃይማኖት ልዩነት ካላቸው ክዋኔው ላይ የሚለየው የሚቀርበው ማእድ ብቻ ነው። ዝምድናውን የጠየቀው ወገን ተጠያቂው እሺታውን ከገለጸ በኋላ በቀጠሮ እለት የዝምድናው ባህላዊ ክዋኔ ሊፈጸም ሲል ዝምድና ጠያቂው ገንፎ ወይም በግ ይዞ ከሚሄዳቸው መካከል ይገኛል። የዝምድና መፈጸሚያ ክዋኔ ከተፈጸመ በኋላ የሚቀርበው ማእድ ዝምድና ጠያቂው ያመጣው ይሆናል። የመጣው ገንፎ ከሆነ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በአንድ መአደ ይቀርባል፤ ይበላል፡፡ በአብዛኛው የጡት ልጅና የጡት አባት ወገኖች አንድ ሃይማኖት ተከታይ ቢሆኑም፣ ባይሆኑም፣ ገንፎ ሁሉንም በአንድ ማዕድ የሚያሰልፍ ምግብ ነው። እንግዶቹ በገንፎ ምትክ ያመጡት በግ ከሆነ የጡት አባት እንዲባርከው ይደረጋል። ዝምድናውን የፈጠሩት ወገኖች ሃይማኖት የተለያዩ ከሆነ የጡት አባት ሌላ በግ ይሰጣል። ስጋው እንዳይተርፍ በአካባቢው ያሉ ጎረቤቶች ይጠራሉ። ከዚህ ውጭ በባህላዊ ክዋኔው ላይ ልዩነት የለም።

በደንቡ መሠረት የጡት መጣባት ዝምድና እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ጋብቻን ብቻ ሳይሆን በዚህ መልክ ዝምድና በፈጠሩት ወገኖች መካከል ጡት መጣባትም የተከለከለ ነው። አንድ ሰው የተለያየ ጎሳ ካላቸው ከአንድ በላይ የጡት ልጆች ወይም የጡት አባት/እናት ሊኖሩት ይችላል። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው የጡት ልጅ ዝምድናው እንደ ጋብቻ ሁሉ ዝምድናን ለማጠናከር በቦታ ቢራራቁም እንደዘመድ ለመጠያየቅ ሲሉ የሚተገበሩት መሆኑን ነው። በዚህ ጥናት መረጃ ከሰጡ ግለሰቦች መካከል ስምንት የጡት ልጅ ያለው ግለሰብ ትልቁን ቁጥር የያዘ ሲሆን ከሁለት እስከ አራት በተለያየ እና በተመሳሳይ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ባህላዊ ክዋኔው ይፈጸማል።

በጡት ልጅነት የሚገኘው ዝምድና በዋናነት ምክንያቱ ጡት ጠቢው ከጡት ተጠቢው ማግኘት የሚፈልገው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ስነልቦናዊ እና የመሳሰሉትን ጠቀሜታዎች ታሳቢ የደረገ ነው።

---

[10] አቶ አለሙ ባጫ ፣ እድሜ 76 የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ(ቃለመጠይቅ)። መረጃ አቀባይ ሲሆኑ በተግባር አራት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ አራት የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ የጡት ልጆች አሏቸው።

በተለይም በአካባቢው ብዙ ዘመን የኖሩና በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ በተለያየ መልኩ ከበሬታን ያተረፉ ግለሰቦች የጡት አባት እንዲሆኑ ይጠየቃሉ። ምክንያቱም የጡት ልጁን በተለያየ መልክ ማጥቃት የፈለገ ወገን ያንን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን የጡት አባቱን እንደደፈረ ያስቆጥረዋል በዚህ መልክ ከለላ የሚፈልጉ ወገኖች የጡት አባት ለምኖ እሺ ከተባለ ስርዓቱን ፈጽሞ ለማንኛውም ጉዳይ ከለላ የሚሆን ዘመድ በባህሉ ደንብ ያፈራል። ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የሚፈልጉ ደግሞ በአካባቢው የሀብት መለኪያ መሰረት ሀብታም ነው ያሉትን ግለሰብ የጡት አባትነት ፈቃድ ጠይቀው ይዛመዳሉ የጡት አባትም ለማንኛውም ዘመዱ የሚያደርገውን እገዛ ያደርግለታል። የጡት ልጅነቱ መመስረቻ ምክንያቶች የተለያዩ ይሆኑና በሂደት ግን ሁለቱ ቤተሰብ ዝምድናውን አጠንክሮ ሲኖር ደጓሚው ተደጓሚ ከለላ ፈላጊው ከለላ የሆኑባቸው አጋጣሚዎች እንደነበሩ ከመረጃ ሰጪዎቹ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ ጡት መጣባት በሥጋ ዝምድና የመተሳሰርን ያህል ባዕዳን በሆኑ፣ በሃይማኖትም በተለያዩ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ማህበራዊ ክፍሎች መካከል አብሮነትን የሚያረጋግጥ መተሳሰብን የሚፈጥር የመቻቻል ገጽታ ነው፡፡ ጡት መጣባት ለሁሉም የህብረተሰቡ አባላት ተሳትፎ ክፍት ወይም የሚያበረታታ ባህላዊ የዝምድና መመስረቻ ስልት ነው። የጡት መጣባት ዝምድና በግለሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሠረተና በራሳቸው ምርጫ የሚከናወን ሰብአዊ ግንኙነት መፍጠሪያ ስልት ነው። ልዩነትን በማክበር መተዋወቅ፣ መቀበል፣ መቀራረብ፣ እንደ ሥጋ ዘመድ መተሳሰር፣ መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ አብሮነት፣ ወዘተ፣ ሁሉ በመርህም በድርጊትም የሚያጠቃልል ልዩ የሆነ ባህላዊ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

### 4.3. ፎክ (ትውፊታዊ) እምነት

'ፎክ-እምነት'፣ 'ትውፊታዊ (traditional) እምነት' ተብሎም ይጠቀሳል (Degh 1972)፡፡ 'ትልልቅ' ተብለው የሚጠቀሱትን፣ ለምሳሌ፡-የክርስትና፣ የአይሁድ፣ የእስልምና፣ የቡድሀ፣ ወዘተ፣ ሃይማኖቶች እምነቶችንም ጨምሮ የሚይዝ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ "የእምነት ሥርዓት የፎክሎር ጥናት ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳብ ነው (Motz 1998:340)። እንደ አንድ የፎክሎር ዓይነት (genre) እምነት … ርዕይዮተ-ዓለምን፣ ሥነ-ኅላዌን (cosmological)፣ የሰማያውይውንና የምድራዊውን አፈጣጠር፣ መንፈሳዊ እምነቶችን፣ ወዘተ፣ ሁሉ የሚያካትት ሰፊ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። ጠበብ አድርገን እንውሰድ ብንል እንኳዋን መናፍስትን፣ መተትን፣ ድግምትን፣ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ሥርዓት-በዐላትን፣ ገድሎችን፣ ተአምራትን፣ ሙዋርትን፣ ባህላዊ ህክምናን፣ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ እምነት የአንድ 'ፎክ' ወይም ቡድን ቁልፍ የመገለጫ ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን ረቂቅ የሆነ የእውቀት ደረጃ ነው፡፡ ስለዚህ ለምርምር (ለጥናት) ተግባር ጠቃሚ የሆኑ የፎክሎር ዓይነቶች በመሆናቸው ተጨባጭ ድርጊቶችንና ባህላዊ መገለጫዎችን መመልከት አለብን በማለት ያስረዳል (Mullen 2000፡ 120-122)፡፡

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ከሃይማኖታዊ ቀኖናዎች ውጭ በጋራ የሚያምኑባቸው፣ በዘልማድ በድርጊት የሚያከናውኑዋቸው፣ በትረካም የሚገልፁዋቸው 'ፎክ' ወይም ትውፊታዊ እምነቶች የጥናቱ ዐቢይ ትኩረት የሆነውን የሃይማኖት መቻቻልን እንዴት ይገልፃሉ በሚለው ላይ ይሆናል፡፡

**ዋቃ (ፈጣሪ) እና አያንቱ(መልእክተኛ)**

ዋቃ ፈጣሪ ማለት ነው፡፡ በማንኛውም የሥነ-ፍጥረት ሚት እንደሚተረከው ሁሉ ዋቃ ምድርንና ሰማይን፣ ጎያውንና ግዑዝ ፍጥረታትን የሠራ ሰማያዊ አምላክ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በሰው እና በፈጣሪ መካከል አገናኝ የሆነ ሰው ደግሞ አያንቱ ይባላል። በትውፊታዊ እምነቱ መሠረት ዋቃና አያንቱ አንዱ የፈጣሪ ሌላው የፍጥረት ግንኙነት አላቸው። አያንቱ የዋቃ ፍጡር ሲሆን ከሌሎቹ ሰዎች የተለየ ስጦታ ያለው፣ በዋቃ የተመረጠ፣ መንፈሱ ያረፈበት፣ ወዘተ፣ ነው ተብሎ የሚታመንበት ወንድ፣ ወይም የሚታመንባት ሴት ነች[ii]።

አያንቱ በዋቃና በአማንያን መካከል እንደ አማላጅ፣ እንደ አገናኝ ድልድይ ሆና ወይም ሆኖ የሚያገለግል መንፈሳዊ መሪ (ritual leader) ነው። አያንቱ የዋቃ መልእክተኛ ሆኖ የሚያማልድ፣ እረኛ፣ ጠባቂ ተደርጎ ይታያል። አንድ አያንቱ ከሌላው አያንቱ የተለየ መንፈሳዊ ኀይል እንዳለው ይታመናል። አያንቱዎች በተሰጣቸው መንፈሳዊ ኀይል አንዱ ከሌላው ይለያያሉ። በአማንያኑ ዘንድ እንደሚታመነው ጉምን ወደ ውሀ የሚለውጥ አያንቱ አለ። ድርቅ በሆነበት ዘመን ወይም ዝናብ ከሚጠበቅበት ጊዜ ሲዘገይ ያዘንባል፡፡ የዝናብ እጥረት ሲከሰት ዝናብ እንዲዘንብ ዋቃን ይለምናል። ሌላው የታመመን ከመድህኒቱ የማገናኘት ኀይል አለው ተብሎ ይታመናል። በእምነቱ መሠረት አያንቱዎች ለማህበረሰቡ የተለያዩ ችግሮችን የሚፈቱ የዋቃ መልእክተኞች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ወደ እነሱ ዘንድ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ችግሩን ለመፍታት ይሄዳል፡፡ አያንቱነት የሃይማኖት ገደብ የለውም። በመሆኑም አንድ የእስልምናም ሆነ የክርስትና(የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ) ሃይማኖት ተከታይ ግለሰብ አያንቱ ሊሆን ይችላል። የአያንቱ ተከታዮችም እንዲሁ ከሁለቱ የአንዱ ሃይማኖት ተከታይ ሆነው ይገኛሉ።

የአያንቱ መንፈስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መንፈስ ሲሆን መራቂው ከተመራቂው ጋር ተወራራሽ መንፈስ አለው። አንጋፋ የሆነ አያንቱ ከሚፈፅመው ሥርዓት መካከል ዋንኛው አዳዲሶችን አያንቱዎች መመረቅና ግዴታዎችን ማሳወቅ ነው። ይህም ለምሳሌ፡- ይህን አታድርግ! ይህንን አድርግ! ለዚህ በሽታ እንደዚህ ዓይነት መድኃኒት ሥጥ፣ ወዘተ፣ የሚሉ መመሪያዎች ይገኙበታል። በዚህ ሁኔታ አንድ አያንቱ መጥፎ መንፈስን ምን ማድረግ እንዳለበት፤ በክፉ መንፈስ(በ'ጂኒ') የተያዘ ሰው ሲመጣ እንዴት እንደሚፈታ፤ እንዴት አጋንንት ማሰር፣ እንዴት ማውገዝ፣ እንዴት መመረቅ፣ ወዘተ፣ እንዳለበት ይማራል፡፡

የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ የሆነው፤ አያንቱ መሆን ከዋቃ የሚሰጥ እንደሆነ ቢታመንም ከታወቁት የሃይማኖት ተቋማት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆንን አይከለክልም። አያንቱ ስለሆነም ከሃይማኖት ተቋሙ አባልነት አለመውጣቱ አንዱ ነው። ሌላው በተለያየ መልኩ በአያንቱ የዋቃ አማለጅነት የሚያምኑ ሰዎች ልክ እንደ አያንቱ የሁለቱ ሃይማኖት ተቋም አባል መሆናቸው እና ሁለቱንም እምነት አብረው ለእነሱ በገባቸው መንገድ አስማምተው ማመናቸው ነው። በአጠቃላይ ከአያንቱ ቤት ሙስሊም፣ ክርስቲያን አለመባሉ ነው። አያንቱ የሚከለከላቸውን ድርጊቶችና እንዲበላ የማይፈቀድለትን ምግብ የእስልምናም ሆነ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች እንዳይበሉ ጥንቃቄ ማድረጋቸው

---

[ii] አያንቱ አለሙ ቱፋ፣አያንቱ ሁሴን፣ አያንቱ ቦንቱ እና አያንቱ ሞቲ (የቡድን ውይይት ሚያዝያ 28/ 2009)

ሌላው የሃይማኖጥ መቻቻል መገለጫ ነው።

አያንቱ ለአማኞቹ አገልግሎት የሚሰጠው በራሱ ግቢ ውስጥ ለብቻ በተሰራ "ገልማ" (ቤት)ነው። 'ገልማ ለዋቃ ምስጋና ማቅረቢያ ወይም የፆሎት ማከናወኛ የጸሎት ቤት('shirine') እንደማለት ነው። የገልማ ባህላዊ አገልግሎት የተቸገረ ወይም አንድ የባህላዊ እምነቱ አካል የሆነ ሥርዓት ለመፈጸም ለሚመጣ ሰው ማስተናገጃ በሳምንት በተወሰኑ ቀናት እንዲሁም በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ምስጋናና መስዋእት ማቅረቢያ ቤት ነው።

የእስልምናም ሆነ የኢ.ኦ.ተ.ቤ አማኝ አያንቱዎች ገልማን በዘልማዶ 'መስጊድ' በሚል ይጠሩታል። ወይም በገልማና በመስጊድ መካከል የተለያየ ትርጉም አይሰጡትም። ገልማዎች በተለይም በገጠር ከሚሰሩት ከማንኛውም ቤቶች በቅርጽ የጎላ ልዩነት የላቸውም። ልዩነቱ በአማኙ አእምሮ ውስጥ ወይም በስተጀርባው ያለው የእምነትና የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት ማከናወኛ ትእምርትነት ነው፡፡

በአያንቱ የሚያምኑ ሰዎች የተለያየ ችግር ሲገጥማቸው ለምሳሌ ሲታመሙ ወይም የቅርብ ሰው ሲታመም፣ የተካካዱ ሰዎች ለመተማመን እና በሌሎችም ምክንያቶች ከተቸገሩት ችግር እንዲያወጣቸው ወይም መፍትሄ እንዲጠቁማቸው በአመቻቸው ወቅት ይሄዳሉ። ከዚህ ውጭ ህጻናት ሲወለዱ ለማስመረቅ እና አያንቱ ዋቃን የሚያመሰግንበት ቋሚ ቀን በአመት አንዴ አንዳንዴ ሁለቴ የታወቀ ቀን አለው በዚህ እለት ከየቦታው በአያንቱ ቤት ይሰባሰባሉ።

አንድ አያንቱ ለዋቃ ግብር የሚያቀርብበት ቋሚ ቀን ሊኖረው ግድ ነው። የአያንቱን ለዋቃ ምስጋና ማቅረቢያ  ቀን የሚወስነው አያንቱነታቸውን መርቆ ያጸደቀው አንጋፋ መንፈሳዊ መሪ ይሆናል። ይህ ቀን ከቅርብም ሆነ ከሩቅ መንገድ አቋርጠው በሚመጡ አማኞች ዘንድ ደምቆ ይከበራል። በዚህ ቀን አያንቱ ዘንድ መጥቶ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ መቅመስ እንደበረከት ይቆጠራል። አያንቱም በዚህ ቀን እከሌና ብሎ መጋበዝ አይጠበቅበትም፡፡ ቀኑን ያስታወሰ የእምነቱ ተከታይ በሙሉ ታዳሚ መሆን ይችላል። እርድ ካለም ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም ለየብቻ ይዘጋጃል። ተጋባዡ ምግቡ ስጋ ከሆነ በመአድ ከመለያየቱ በስተቀር ተቀላቅለው አንዱ በጠጣበት የቡና ስኒ ሌላው እየጠጣ ይገባበዛል። በዚህን ቀን ቀደም ብለው ስዕለት ተስለው የተሳካላቸው እንደ ስእለታቸው አይነት ይዘው ይመጣሉ። ስዕለቱ የሚታረድ ከብት፣ የተዘጋጀ ምግብ የሚፈላ ቡና የሚጨስ እጣን ወይም ሰንደል እና መሰል ነገሮች ከሆኑ በዚሁ ዕለት አገልግሎት ላይ ይውላል። ለቀጣዩ አመት ክብረ በአልም የሚሳሉ ካሉ ሰው በተሰበሰበበት ወይም በአርምሞ የሚሳሉ የእምነቱ ተከታዮች አሉ።

ከአያንቱ ጋር የተያያዙ በእስልምናም ሆነ በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች በተናጠል ባለጉዳዮቹ ብቻ ወደ አያንቱ በመሄድ ከሚከበሩ ባህላዊ ሥርዓተ-ክዋኔዎች አሉ። እነዚህም አርባ ቀን ያልሞላቸው ህጻናት በቤተሰቦቻቸው አማካይነት ተወስደው የሚመረቁበት ሥርዓተ- ክዋኔ ሀሙቺሳ ይባላል። ሀሙቺሳ ማለት ማሳቀፍ እንደማለት ነው። ህጻናቱ ሲመጡ ይዘው የሚመጡት የተለያየ የምግብ አይነቶች እጣን ወይም ሰንደል ቡና እናም ሌላም ለመመረቂያ የሚሆኑ ስዕለትም ካለ አብሮ መጥቶ አያንቱ ለዋቃ ምስጋና በማቅረብ ህጻኑን አቅፎ ይመርቃል። መጠርያ ሥም ያወጣሉ። ሌላው ሥርዓተ ክዋኔ ለሙሽሮች የሚደረግ ምርቃት ነው። እንዲሁም በስዕለት የተወለዱ ልጆች ለጋብቻ ደርሰው ሊያገቡ ሲሉ በሰርጉ ዋዜማ ወይም

ቀደም ብሎ አያንቱ ዘንድ በመሄድ የሚመረቁበት ነው።

በአጠቃላይ ባህላዊ እምነቶችና ሥርዓተ-ክዋኔዎች በኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚካሄዱ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ እነዚህም በአብሮ መኖር ሂደት ውስጥ የገነቡትን የመቻቻል እሴቶች የሚያሳዩ ክዋኔዎች ናቸው። ከዚህ ውጭ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ባህላዊ እምነቶቹን እንደሁዋላቀር ልማድ ይመለከታሉ። በመሆኑም አማኞቹ በግልፅ ሲያከናውኑዋቸው አይታዩም፡፡ ባህላዊ እምነቶችን ከዋናው ሃይማኖታቸው ጎን ለጎን የሚያከናውኑት የእስልምና እና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በሁሉም የአምልኮ ሥፍራዎች የሚሳተፉት የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን ልብ ማለት አስፈላጊ ይሆናል።

የአያንቱ አምልኮ እንደ ማንኛውም እምነት በለውጥ ሂደት ውስጥ ይገኛል፡፡ ለውጡ ሁለት መልኮች አሉት። አንደኛው ለውጥ የክርስትናውም ሆነ የእስልምናው አስተምህሮ እየጠነከረ መሄድ። የሁለቱ ሃይማኖት መምህራን በየመድረኩ "ባእድ አምልኮ ነው" በሚል አማኞቹ ትክክል እንዳልሆኑ መስበካቸው ዋንኛው ምክንያት ነው። በዚህም ምክንያት በተለይ ወጣቶቹ ቤተሰቦቻቸውን በመቃወም "የአያንቱ መንፈስ ትክክል አይደለም" በማለት እምነቱን እያጣጣሉ፤ ጠንከር ሲልም ገልማዎቻቸው ድረስ በመሄድ የረበሹበት አጋጣሚ እንደነበር ከአያንቱዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል። ሌላው ለውጥ አያንቱዎች ተሰባስበው ከተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ለመከላከል እና እንደ አንድ የእምነት ተቋም እውቅና ጠይቀው ያገኙበት ነው። ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በመንግሥት እውቅና ተሰጥቶት "የአያንቱ መላከ ውቃቢ[12] እምነት" ተብሎ እንደ አዲስ እምነት ተቋቁሟል። "የአያንቱ መላከ ውቃቢ እምነት" ልዩ ገጽታው የእምነቱ መስራች አባላት የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የሙስሊም ሃይማኖት ተከታይነታቸውን ሳይተው የዚህ እምነት መስራችና ባለቤት መሆናቸው ነው።

## 4.ማጠቃለያ እና ይሁንታ

በአጠቃላይ በተይም በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ለረዥም ጊዜ አብሮ በመኖር ሂደት የተፈጠሩና ሥርፀት ያገኙ ፎክሎራዊ የመቻቻል ባሕርያት መገለጫዎችንና የተለያዩ ምግባራዊ እሴቶች ምን እንደሚመስሉ፣ ምን ማህበራዊ ተግባር እንደሚያሙዋሉና እንዴት እንደሚገለፁ ተመልክተናል፡፡ ምግባራዊ እሴቶቹ በአንድ በኩል ከገሀዱ ዓለም ሕይወት ወይም የአኑዋኑዋር ስልትና ፍልስፍና የመነጨና የተቃኙ ሆነው እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቦቹ መካከል ያሉትን የሃይማኖት ልዩነቶች በመቻቻል የሚመሩ፣ በባህል የተደነገጉና የተቋዋቋዋሙ ለዘላቂ ሰላም መሠረትና ዋስትና ተግባራዊ ሕጎች ሆነው ይሠራሉ፡፡ እንደተመለከትነው እሴቶች ወይም የመቻቻል ባሕርያቱ በተለይም በእስልምናና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል 'መቻቻል' የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ፣ መርህና ተግብራዊ ድርጊቶች በአጠቃላይም እውነተኛ ትርጉም የሚያካትቱ ገጽታዎችን፣ ማለትም፡- አንዱ የሌላውን ኅልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣ መከባባርን፣ መተሳሰብን፣

---

[12] "መላከ" የሚለው ቃል እንዲለወጥ የተለያዩ አካላት ስለጠየቁ ቃሉ በሌላ እንደሚተካ ወይም እንደሚቀር ጠቁመዋል።

መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንና ሰላምን፣ ወዘተ፣ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በአንፃሩ ሲታይ እነዚህ በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ አማንያን መካከል ሥር የሰደዱ የመቻቻል መገለጫ ባሕርያት በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ ሥርፀት አግኝተዋል ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም።

በሃይማኖታዊ አውድ ውስጥ መቻቻልን ለመረዳት ስንሞክር በመጀመሪያ በአእምሮአችን የሚፈጠረው ለጎልውና አስፈላጊ በሆነ በባህል ተቀባይነት ባለው ደንብ ላይ የተመሠረተ የአለመቀበል (rejection) ዋነኛ ጥያቄ የሆናል፡፡ እንዲህ ያለው አለመቀበል ለሁሉም የቻይነት (tolerant) ባሕርያት ዓይነቶች አስፈላጊ ሁኔታ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚያም፡- "የሌሎችን ሰዎች እምነት በሚመለከት በዘወትራዊ ሕይወት መቻቻልን በገቢር የምንተረጉመው ተቀባይነት ባላቸው ተገቢ ምክንያቶች የማንቀበለው ነገር መኖሩንም ጨምረን ከገለፅን ነው፡፡ የሌሎችን ሀሳቦች፣ እምነቶች፣ አመለካከቶች፣ ድርጊቶች ጨርሶ የማንቀበል ከሆነ፣ እንዲሁም 'ሌላነት' ('otherness') የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ ያለውን እሴት (ጥቅም) የማናደንቅ ከሆነ 'ቻይነት' አያስፈልገንም" (Habermas 2004፡ 10) በማለት ያጠቃለለው ሀሳብ፣ በአንድ በኩል፣ በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች የሚታዩትን ልዩነቶች፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በእስልምና እና *በኢ.ኦ.ተ.ቤ* መካከል የዳበሩትን የመቻቻል ባሕርያት ደረጃና ሥርፀት የሚገልፅ ይሆናል፡፡

ጥናቱ ከጅምሩ ይዞት የተነሳው ዐቢይ ዓላማ በተጠቀሱት ማህበረሰቦች መካከል ለረዥም ዘመናት አብሮ በመኖር ሂደት በማንኛውም ገቢራዊ የሕይወት ገጽታ የተፈጠረውንና ሥርፀት እያገኘ የመጣውን የመቻቻል ባሕርያትንና የመገለጫ ዓይነቶችን ወይም ቅርፆችን ለመመርመር፣ ለመግለጽና ይህንንም ለሌሎች እንዲያውቁት በጥናት ላይ ተመስርቶ በመጻፉ ማስተዋወቅ ነው። ከዚህም ባለፈ ለሰላማዊ አብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸውን የሃይማኖት መቻቻል ለማስተዋወቅ የሚመለከታቸው አካላት ማን ምን ያድርግ የሚለውን በይሁንታ ተጠቁመዋል።

### ይሁንታ

አጥኚዋ የጥናቱን ውጤት መነሻ በማድረግ በቀጣይ ቢደረግ የምትለው።

1.ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሃይማኖት መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶች እውቅና ማሰጠት ቢችል፣

2.ከታሪክ አንጻር ለማስተማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ሲደረግ መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶን በምንባብ ውስጥ አስገብቶ እግረመንገድ መልካም እሴቶችን ለማያውቋቸው ታዳጊ ልጆች ማስተዋወቅ ቢቻል፣

3.የተለያዩ ባህላዊ ትርኢቶችን የሚያዘጋጅ ክፍል እነዚህን ባህላዊ ጭብጦች መነሻ ሀሳብ አድርገው እግረመንገድ ቢያስተዋውቋቸው፣

4.ባህል ሕዝብን እንዴት ማስተሳሰርና ማስተዳደር እንደሚችል የርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ ፖለቲከኞች ግንዛቤ መስጠት ቢቻል።

### ዋቢ ጽሁፎች(References)

ደስታ ተክለ ወልድ። 1962*አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ።

የበቆጂ ከተማ ሁለተኛ ሸንጎ። 1988።"*የመተዳደሪያ* ውስጠ ደንብ(*ያልታተመ*)።

የሌሙና ቢልቢሎ *ወረዳ* አስተዳደር።2002።አጠቃላይ *መረጃ*።(*ያልታተመ*)።

Abbink, Jhon; 1998; *An Historical-anthropological approach to Islam in Ethiopia*: Issues of identity and politics; Journal of African cultural studies, Volume11, Leiden.

Abdullah, T. 2012. "*Co-existence and Harmony in a pluralistic world: Gulen movement as wording model,"* a paper presented at a conference on establishing and sustaining the culture of co-existence and mutual understanding organized by ministry of Federal Affairs.

Braukamper, Ulrich. 1992; *Religious Syncretism in Southern Ethiopia, Journal of* religion in Africa, Vol. 22, No. 3, pp. 194-207.

Federal Democratic Republic of Ethiopia, 2009; Central Statistical Agency; *2007 Population & Housing Census of Ethiopia*; Addis Ababa.

Motz, Marilyn. 1998. *The Practice of Belief*, Journal of American Folklore 111:339-355,

Fetterman, D.M. 2009. *Ethnography: Step-by-Step* (3rd ed), New Deli, Saga publication, inc.

Habermas, JÜrgen.2004."Tolerance: The Pacemaker for Cultural Rights", Journal of Philosophy, vol. 79, No 30.

Mullen, B.; 2000; *Belief and the American Folk. Journal of* American Folklore, 113(448):119-143.

Murphy, Andrew. 1997. "Toleration, and Liberal Tradition,"Journal of Polity, vol. 29, No. 4, pp. 593-623.

Newman, Jay. 1978. "The Idea of Religious Tolerance". Journal of American Philosophical Quarterly,Vol. 15, No. 3, pp 87- 195.

UNESCO; 1995; *Declaration of principles on Tolerance* proclaimed and signed by the Member States of UNESCO on 16 November 1995, Paris: UNESCO.